# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# ኤርሚያስ ፣ የእንባ ሰው፡፡




ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Jonathan Hay

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): Mary-Anne S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia



አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org



©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ኤርሚያስ በይሁዳ አገዛዝ ፣ በሐይማኖተኛ ቤት ውስጥ የተወለደ ሰው ነው፡፡ አባቱ ኬልቂያስ ካህን ነበረ፡፡ ቤተሰቡ ከኢየሩሳሌም ብዙ በማይርቅ አናቶት በሚባል ከተማ ውስጥ ይኖሩ ነበረ፡፡ ምንአልባት ፣ የኤርሚያስ ወላጆች እርሱም ካሕን ይሆናል ብለው ያስቡ ነበረ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ሌላ እቅድ ነበረው፡፡




በኤርሚያስ ውልደት ወቅት ፣
የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ
እግዚአብሔር ቃል አይመላለሱም
ነበረ፡፡ አብዛኛው ሰው ፣ ከንጉሱ
ጀምሮ እስከ ታች ያለው ባሪያ ድረስ
፣ የሐሰት አምላክን ያመልኩ ነበረ ፤
በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ
እንኳን ሳይቀር፡፡
3


ኤርሚያስ ወጣት
እያለ ፣ እግዚአብሔር
እንዲህ ሲል ተናገረው ፤
“ሳትወለድ አስቀድሞ
አውቄሃለሁ፡፡” እግዚአብሔር ለኤርሚያስ
አለው ፣ “ስለ እኔ ትናገር ዘንድ አቅጄአለሁ፡፡”
4


የእግዚአብሔር ጥሪ ለኤርሚያስ የሚያስፈራ ይመስል ነበረ፡፡ እንዲህ ብሎ
ጮኸ “አ! እግዚአብሔር አምላክ!”፡፡ “እኔ ገና ልጅ ነኝና ፣ መናገር
አልችልም፡፡” ከሃያ አመት ያለፈ ትልቅ ሰው ነበረ፡፡ ነገር ግን ኤርሚያስ
በከበበው ክፉ ላይ ስለ እግዚአብሔር ለመናገር እንደሚችል አላሰበም ነበር፡፡
5


እግዚአብሔር ኤርሚያስን እንዲህ ሲል አረጋገጠለት ፤
“አትፍራ፡፡” “ወደ ምልክህ ሁሉ ሒድ ፤ ተናገር
የምልህን ሁሉ ነገር
ተናገር ፤ እኔ
ከአንተጋ ነኝና
አድንሃለሁ፡፡”
ከዚያም እግዚአብሔር አንድ ልዩ
ነገር አደረገ፡፡ እግዚአብሔር
የኤርሚያስን አፍ ነካው፡፡
6


እግዚአብሔር ለኤርሚያስ ጥንካሬ ፣ ድፍረትና ጥበብን ሰጠው፡፡
በድፍረትም እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን ፍቅርና ረድኤት ተናገረ ፤ ነገር
ግን ማንም እርሱን አልሰማውም ፤ ንጉሱንም ጨምሮ፡፡
7


ካህናቶቹ ሳይቀሩ ተናደዱና ንግግሩን እንዲያቆም ነገሩት፡፡ ኤርሚያስ
የሚናገረው ነገር የተሳሳተ እንደሆነ የሚናገሩ ሐሰተኛ ነብያትም ነበሩ፡፡
8



ኤርሚያስም ሕዝቡን ከመቶ አመታት በፊት ሰሜኑ የእስራኤል ክፍል እግዚአብሔርን እንደተወ አሳሰባቸው፡፡ አሶራዊያን የሆኑ ጠላቶቻቸው አሸንፈዋቸው ከእስራኤል ውጪ ሩቅ ወደ ሆነ ስፍራ ወሰዱአቸው፡፡
9
ከዚያም የይሁዳ ሕዝብ ፣ የደቡቡ ክፍል ፣ እንደገና እግዚአብሔርን ተወ፡፡ የጠላት ሰራዊት ከብበዋቸው ነበረ፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲሸነፉና እንዲማረኩ አሳልፎ ይሰጣል?
10
ሕዝቡ ጣኦቶቻቸውን ያምኑ ነበረ፡፡ ጣኦቶች ከጠላቶቻቸው እጅ ሊያድኑአቸው ይችላሉ? በፍጹም ! እግዚአብሔር ብቻ ነው ሊያድናቸው የሚችለው፡፡ ሕዝቡ በኤርሚያስ ላይ እጅግ ተቆጣ፡፡ ሊገድሉትም ያሴሩ ጀመረ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር አገልጋዩን ጠበቀው፡፡
11
በመጨረሻም ፣ እግዚአብሔር ኤርሚያስን ያስደነገጠውን አንድ ነገር አደረገ፡፡ እግዚአብሔርም እንዲህ አለ ፣”ለዚህ ሕዝብ አትጸልይ ፤ እርዳታን ፈልገው ሲጮሁ እኔ አልሰማቸውም፡፡”
12
ኤርሚያስም ንጉሱን ከባቢሎንጋ ያለውን ጦርነት እንደሚሸነፍ ነገርው፡፡ ንጉሱ እጅግ ስለተቆጣ ፣ ኤርሚያስን በወሕኒ ውስጥ ወረወረው፡፡ በወህኒም ውስጥ ሆኖ ኤርሚያስ ስለ እግዚአብሔር ይሰብክና እግዚአብሔርን ያምን ነበረ፡፡
13
ከወሕኒ ቤት ከወጣ በኋላ ፣ ኤርሚያስ እንደገና ለንጉሱና ለሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ እምነታቸውን በእርሱ ላይ እንዲያደርጉ ይሰብክ ነበረ፡፡ በዚህኛው ጊዜ ፣ ንጉሱ ኤርሚያስን ጨለማ ወደሆነ ስፍራ ወረወረው፡፡
14

ነገር ግን እግዚአብሔር በንጉሱ ልብ ውስጥ በስራ ላይ ነበረ፡፡ ኤርሚያስን በድብቅ አስፈታውና እግዚአብሔር ንጉሱን ምን እንዲያደርግለት እንደሚፈልግ ጠየቀው፡፡ “ወደ ምርኮ ሒድ! በዚያ ትኖራለህ፡፡” የሚል መልስ ነበረ የሰጠው፡፡



15

የባቢሎናዊያን ሰራዊት ኢየሩሳሌምንና ይሁዳን ሁሉ ተቆጣጠሩ፡፡ ቅጥሩን እያፈራረሱና ግንቦቹም እየናዱ ሁሉን ነገር ያቃጥሉ ነበረ፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡ ለሰባ አመታት ወደ ምርኮ እንደሚሄድና ከዚያም በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር መልሶ እንደሚያመጣቸው ይናገር ነበረ፡፡



16

ኤርሚያስ ፣ የእንባ ሰው፡፡

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

ኤርሚያስ

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት** 119:130

17

# መጨረሻ

28 60

18

**ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።**

**እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።**

**ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት**
**ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።**

**በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር!** **የሐ.** 3.16

19